# በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማዕ/ጎሀ/ስ ለደብረ ኀይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ካቴድራል የተሰጠ

## የምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ኮርስ




አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍት ብሉያት፣ የመጻሕፍት ሊቃውንትና የመጻሕፍት መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ሰኔ ፳፬፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም

# ምስጢራተ ቤተክርስቲያን

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በተለያየ ሁኔታ ሲገለጥና ስጦታውን ሲያድል ኖሯል ይኖራልም፡፡ ሰዎች በትምህርትም በመገለጥም አማካኝነት እግዚአብሔርን ወደማወቅ ይደርሳሉ፡፡ ስብከት/ትምህርት ላላመኑት ሁሉ የሚሰበክና ላመኑት ደግሞ ማጽኛ ነው፡፡ የሰው ልጅ ለመዳን ማመን ይገባዋል፡፡ እምነት የድኅነት መግቢያ በር እንጂ በራሱ ድኅነት አይደለም፡፡ በር ያሰኘውም ያለእምነት ወደየትኛውም መንገድ መሄድ ስለማይቻል ነው፡፡ የመዳናችን ጉዳይ እስከሞት ድረስ በሂደት ላይ የሚገኝ መንፈሳዊ ትግል ያለበት ክርስቲያናዊ የሕይወት ጉዞ ነው፡፡ በጸጋው መዳን ማለት ምሥጢራትን በመፈጸም መዳን ማለት ነው፡፡ ጸጋው ምሥጢራትን ሳይፈጽሙ አይገኝምና፡፡ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የሚባሉት የክርስቶስን ጸጋ በእምነት የምንቀበልባቸው ስጦታዎች ናቸው፡፡ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ከሚባሉት ጥቂቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ምስጢረ ጥምቀት
- ምስጢረ ሜሮን
- ምስጢረ ቊርባን
- ምስጢረ ክህነት
- ምስጢረ ተክሊል
- ምስጢረ ንስሓ
- ምስጢረ ቀንዲል

ከእነዚህ መካከል ጥምቀት፣ ተክሊልና ክህነት የማይደገሙ ሲሆኑ ሜሮን፣ ቊርባን፣ ቀንዲል እንደ አስፈላጊነታቸው የሚደገሙ ናቸው፡፡

## ለምን ምስጢር ተባሉ?

በሃይማኖት ምስጢር የሚባለው በእምነት ከመቀበል በስተቀር የሰው አእምሮ መርምሮ የማይደርስበት የአምላክ ሥራ ነው፡፡ ከላይ ያየናቸው ምስጢራት ምስጢር የተባሉት በዓይን በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ እግዚአብሔር የሚያስገኙ በመሆናቸውና ጸጋው በምስጢራቱ አማካኝነት ለምእመናን ሲሰጥ ስለማይታይ ነው፡፡

## ምስጢረ ጥምቀት

ጥምቀት የምስጢራት ሁሉ መጀመሪያ ነው፡፡ ጥምቀት የሚለው ቃል አጥመቀ-አጠመቀ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሳቢ ዘር ሲሆን ትርጉሙ በገቢር መንከር፣ መድፈቅ፣ መዝፈቅ ማለት ሲሆን በተገብሮ ደግሞ መነከር፣ መዘፈቅ፣ መደፈቅ ማለት ነው፡፡ ጥምቀት ከሌሎች ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ለመሳተፍ መግቢያ በር ነው፡፡ በጥምቀት ከእግዚአብሔር የጸጋ ልጅነትን ተቀብለን የቤተክርስቲያን አባል እንሆናለን (ዮሐ.3፥5፤ ሮሜ 6፥3-5)፡፡ በመጠመቃችን ከክርስቶስ ጋር አንድ እንሆናለን፡፡ ትንሣኤ ልቡናን፣ በጎ ኅሊናን፣ አዲስ ሕይወትን ከእርሱ እናገኛለን፡፡ ጥምቀትን የመሠረተው ራሱ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ከዚያም ሐዋርያት አጥምቀው እጃቸውን በተጠማቂው ላይ በመጫን መንፈስ ቅዱስን ያሳድሩ ነበር (የሐዋ. ሥራ 8፥14-17)፡፡ በጥምቀት ሥርየተ ኃጢአት (የሐዋ. ሥራ 2፥37)፣ ዳግም ልደት/ሐዲስ ተፈጥሮ (ዮሐ.3፥5፣ 1ኛ ዮሐ.3፥1፣ ሮሜ 8፥16፣ ሮሜ 6፥3) ይገኛል፡፡

## የጥምቀት ምሳሌዎች

- ❖ ማየ አይኅ (ዘፍ.6፥7)
- ❖ ግዝረት (ዘፍ.17፥14)
- ❖ ባሕረ ኤርትራ (ዘፀ.14፥21-25)
- ❖ ፈለገ ዮርዳኖስ

## የጥምቀት ዓይነቶች

አማናዊ ልጅነት የሚገኝባቸው የጥምቀት ዓይነቶች አራት ናቸው፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ➢ የውሃ ጥምቀት
- ➢ የደም ጥምቀት
- ➢ የእሳት ጥምቀት
- ➢ የእንባ ጥምቀት

የውሃ ጥምቀት የሚባለው ካህኑ ውሃ አቅርቦ ሲጸልይበት ውሃው በዕለተ ዓርብ ከክርስቶስ ጎን የፈሰሰውን ውሃ (ማየ ገቦ) ይሆናል፡፡ በዚያ ተጠምቀን ልጅነትን እናገኛለን ማለት ነው፡፡ የደም ጥምቀት የሚባለው አንድ ሰው በክርስትና ሃይማኖት አምኖ ከመጠመቁ በፊት ሰማዕት ቢሆን ደሙ ጥምቀት ይሆነዋል ማለት ነው፡፡ በእሳት ተጥሎ ከሞተ ደግሞ እሳቱ ከጥምቀት ተቆጥሮለት የእሳት ጥምቀት ተጠመቀ ይባላል፡፡ የእንባ ጥምቀት የሚባለው ደግሞ አንድ ንዑሰ ክርስቲያን ለመጠመቅ በዝግጅት እያለ ቢሞት እንባው ጥምቀት ይሆነዋል ማለት ነው፡፡

## መች እንጠመቃለን?

የሕፃናት ጥምቀት ወንድ በተወለደ በአር ቀኑ፣ ሴት በተወለደች በ80 ቀኗ ይጠመቃሉ፡፡ ከጥምቀታቸው በፊት ለሞት የሚያደርስ ሕመም ቢያጋጥማቸው በሞግዚት አማካኝነት ከተጠቀሰው ቀን በፊት መጠመቅ ይችላሉ፡፡ አንዲት እናት አንድ ወንድና አንዲት ሴት መንታ ልጆችን ብትወልድ ወንዱ በሞግዚት በአርባኛው ቀን ሲጠመቅ ሴቷ ደግሞ በ80ኛ ቀኗ ከእናቷ ጋር ሄዳ ትጠመቃለች፡፡ ሌሎች ባመኑበት ጊዜ አምስቱን አዕማድ ተምረው ይጠመቃሉ፡፡ እናት ከወለደች በኂላ ሄደን ብንጠይቃት፣ ሰላም ብንላት ምንም የሚያረክሰን ነገር የለም፡፡ በዚያኑ ቀን ወደ ቤተክርስቲያን መግባት እንችላለን፡፡

## በማን ስም እንጠመቃለን?

ማንኛውም ሰው በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ይጠመቃል (ማቴ.28፥19)፡፡ ሐዋርያት በኢየሱስ ስም እንዳጠመቁ ተጽፏል (የሐዋ. ሥራ 2፥38)፡፡ ይኸውም ሦስቱ አካላት በግብረ ባሕርይ አንድ ስለሆኑ የአንዱ ስም ከተጠቀሰ ሁለቱንም የሚመለከት መሆኑን በመረዳት ያደረጉት ነው፡፡

## ምስጢረ ሜሮን

ሜሮን ቃሉ የጽርዕ ሲሆን የሚጣፍጥ፣ ልብ የሚመስጥ፣ መዓዛ ያለው ቅዱስ ቅባት ነው፡፡ ከተለያዩ ዕፀዋት ተቀምሞ ይዘጋጃል፡፡ ከጥምቀት ቀጥሎ ወዲያው የሚፈጸም ምስጢር ነው፡፡ ሰው በውሃ ተጠምቆ በሜሮን ሲቀባ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ይታደላል፡፡ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሙሴን የተባረከ ቅዱስ ዘይት ከተለያዩ ዕፀዋት እንዲቀምም አዝዞት ነበር (ዘፀ.30፥25-32)፡፡

በዘመኑ የነበረው አገልግሎትም ቤተመቅደስንና ንዋያተ ቅድሳትን ማክበር፣ ካህናተ ኦሪትን መለየትና መቀደስ ነበር፡፡ ምስጢረ ሜሮን አበው ሐዋርያት የሠሩልን ሥርዓት ነው፡፡

## የሜሮን ምሳሌዎች

- ያዕቆብ በሐውልቱ ላይ የቀባው ዘይት (ዘፍ.28፥1)
- የሙሴ የተቀደሰ ዘይት (ዘፀ.30፥31)

በአንብሮተ እድ ፋንታ ተጠማቂዎች ሜሮን እንዲቀቡና ሀብተ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ በሎዶቅያ ጉባኤ ተወሰነ (ዶቅ.48)፡፡ ተጠማቂዎች 36 የአካል ክፍሎቻቸውን በሜሮን ይቀባሉ፡፡

## የሜሮን አቀባብ

ሜሮኑን ካህኑ ይዞ መጽሐፈ ክርስትናን እያነበበ ይጸልያል፡፡ የሜሮን መያዣውን እቃ ከፍቶ በቀኝ እጁ አውራ ጣት ከድኖ በመዘቅዘቅ ጣቱን ያስነካዋል፡፡ ዲያቆኑም ተጠማቂውን ራሱን ዝቅ አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት እንዲቆም ያደርጋል፡፡ በመቀጠል ካህኑ ሜሮኑን ይዞ በተጠማቂው ላይ ይጸልያል፡፡ ከዚያም የተጠማቂውን 36 ሕዋሳት በትእምርተ መስቀል ይቀባል፡፡ ሕዋሳቱም፡-

- ግንባሩን ግራና ቀኝ (2)
- የአፍንጫውን በር ሁለቱን (2)
- ሁለቱን ከንፈሮቹን (2)
- ጆሮዎቹን (2)
- ዐይኖቹን (2)
- ደረቱን (1)
- ልቡን (1)
- ከመሐል አናት እስከ ወገብ (1)
- እንብርቱን (1)
- እጆቹን (2)
- የእጆቹን መገናኛዎች (2)
- ትከሻዎቹን (2)
- ማጅራቱን (1)
- አንገቱን (1)
- ክርኖቹን (1)
- የእጆቹን ውስጣዊና ውጫዊ ክፍሎች/መዳፎች (4)
- የእግሩን መገናኛዎች
- ጉልበቶች (2)
- የእግሮቹ ውስጣዊና ውጫዊ ክፍሎች (4)

አካለ መጠን ያደረሰች ሴት ስትጠመቅ ካህኑ ዕርቃኗን እንዳያይ ፊቱን በሻሽ ተሸፍኖ ዲያቆናዊት ሴት እጇን ይዛ ትቀባለታለች፡፡

## ምስጢረ ቊርባን

ቊርባን ቃሉ የሱርስት ሲሆን ትርጉሙ በቊሙ መንፈሳዊ አምኃ (ስጦታ)፣ መሥዋዕት፣ መባዕ፣

ለአምላክ የሚቀርብ እና የሚሰጥ ገንዘብ ነው፡፡ በሐዲስ ኪዳን የምናቀርበው ቊርባን ከሰማይ የወረደውን የሕይወት እንጀራ የእግዚአብሔር ቃል የተዋሐደው ሥጋ ነው (ዮሐ.6፥51-58)፡፡ የምስጢራት ሁሉ መፈጸሚያቸው ምስጢረ ቊርባን ነው፡፡

## የምስጢረ ቊርባን ምሳሌዎች

- ✓ መሥዋዕተ መልከ ጼዴቅ (ዘፍ.14፥18)
- ✓ የእስራኤል ፋሲካ (ዘፀ.12፥3-11)

የምስጢረ ቊርባን መሥራች ራሱ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማቴ.26፥26)፡፡

## በምስጢረ ቊርባን የሚገኝ ጸጋ

- ❖ የዘለዓለም ሕይወትን ይሰጠናል (ዮሐ.6፥53)
- ❖ ሥርየተ ኃጢአትን ያስገኛል (ማቴ.26፥27)
- ❖ ወደ ቅድስናና ወደ ጽድቅ ይመራናል (ዮሐ.6፥35)

## ምስጢረ ክህነት

እግዚአብሔር በአገልጋዮች አድሮ ጸጋን ስለሚያድልበት ምስጢር ተብሏል፡፡

## ምስጢረ ቀንዲል

ቀንዲል የሚለው ቃል ካንድል (Candle) ከሚለው የላቲን ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም መብራት ማለት ነው፡፡ ምስጢረ ቀንዲል ሕመምተኞች በሃይማኖት ከአካላዊና ሥነ ልቡናዊ ሕመም እንደሚፈወሱ የሚናገር ነው፡፡ የሚፈጸመውም በካህናት አማካኝነት ነው፡፡ ካህናት መብራት አብርተው፣ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መጽሐፈ ቀንዲልን ዘርግተው ይጸልያሉ (ያዕ.5፥14) በምስጢረ ቀንዲል ፈውሰ ሥጋ ፈውሰ ነፍስ ይገኛል፡፡ ቀንዲል የሚፈጸምለት ሰው መጀመሪያ ኃጢአቱን መናዘዝ አለበት፡፡ ከዚያ ካህናቱ ንጹሕ ዘይት አቅርበው በየተራ በሰውየው ራስ ላይ ወንጌል ያነባሉ፡፡ ከዚያ ሰባቱም እጃቸውን በራሱ ላይ ጭነው ይጸልዩለታል፡፡ በመጨረሻም በጫፋቸው ጥጥ የተጠመጠመባቸው ሰባት እንጨቶችን ይይዛሉ፡፡ ይህንን በየተራ ወደተጸለየበት ዘይት እየነከሩ በትእምርተ መስቀል ይቀቡታል፡፡ አምስቱን ሕዋሳት ማለትም ዐይኑን፣ ጆሮውን፣ አፉን፣ አፍንጫውን፣ እጁን ይቀቡታል፡፡ ምስጢረ ቀንዲልን መፈጸም የሚችሉት በቤተክርስቲያን ሥርዓት የቅስና መዓርግና ከዚያ በላይ መዓርግ ያላቸው አባቶች ብቻ ናቸው፡፡

## ምስጢረ ተክሊል

ከለለ-ከለለ፣ አከበረ፣ ጋረደ ከሚለው የግእዝ ግሥ ተክሊል የሚል ባዕድ ዘር ይወጣል፡፡ መከበሪያ፣ ማክበሪያ፣ ማስከበሪያ፣ መከባበሪያ፣ ማከባበሪያ፣ ክብር እያለ በሰዋስው ይተረጎማል፡፡ ድንግልናቸውን ጠብቀው የቆዩ ሙሽሮች ሲጋቡ የሚከናወን ሥርዓት ነው፡፡ ምስጢር መባሉ በሥጋ ወደሙ አማካኝነት አንድ ስለሚሆኑ ነው፡፡ አንድ መሆናቸውም ልጅ በመውለድ ነው፡፡ ጋብቻ የተጀመረው በአዳምና በሔዋን ነው፡፡ የጋብቻን ክቡርነት ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ተገኝቶ ተአምር በማድረግ አስረድቷል፡፡ የጋብቻ መሠረታዊ ዓላማዎች፡-

- ○ ለመረዳዳት (ዘፍ.2፥18)
- ○ ዘር ለመተካት (ዘፍ.1፥28)

- ○ ከዝሙት ለመጠበቅ (1ኛ ቆሮ.7፥17፤ ዕብ.13፥3)

## የጋብቻ ምሳሌዎች

- የእግዚአብሔርና የቤተ እስራኤል አንድነት (ሆሴ.2፥16)
- የክርስቶስና የቤተክርስቲያን አንድነት (1ኛ ዮሐ.3፥17)

በሃይማኖት የማይመስለንን ወይም የማትመስለንን ማግባት፣ የቅርብ ዘመድን ማግባት አይፈቀድም። ደናግላን በሥርዓተ ተክሊል ሲጋቡ ደናግላን ያልሆኑ ደግሞ በጸሎተ መዓስባን ይጋባሉ።

## ምስጢረ ንስሓ

ንስሓ ሊሠሩት በማይገባ ሥራ ወይም ኃጢአት ማዘን፣ ምነው ባልሠራሁት ምነው ባላደረግሁት ብሎ ማዘን፣ መጸጸት፣ መቆጨት ነው። ንስሓ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቂያ መንገድ ነው።

## በንስሓ የሚገኙ ጸጋዎች

- ሥርየተ ኃጢአት (ኤር.31፥34)
- ከእግዚአብሔር መታረቅ (ሉቃ.15፥11-32)
- ፍጹም ሰላም (ዮሐ.14፥26)

በንስሓ የተመለሰ ሰው ኅሊናው ከጸጸት የጸዳ ስለሚሆን ልቡ ፍጹም ሰላምን የተመላ ነው። ሰው ንስሓ ሲገባ ወይም ሲናዘዝ በኀልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር የሠራውን ኃጢአት፣ የበደለውን በደል ሳይጨምር ሳይቀንስ መናገር ነው። ካህኑ ለተነሳሒው የሚሰጠው መንፈሳዊ ቅጣት ቀኖና ይባላል። የሚሰጠው ቀኖና የጾም፣ የጸሎት፣ የስግደት፣ የምጽዋት ሊሆን ይችላል። ንስሓ በማናቸውም ጊዜ መግባት ይቻላል። የቀኖናው ዓይነት ግን እንደየወቅቱ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ በበዓለ ኀምሳ መስገድ፣ መጾም አይቻልም። ስለዚህ ከስግደትና ከጾም ውጭ የሆነ ቀኖና ሊሰጥ ይችላል። ንስሓ ገብተን፣ ቀኖናችንን ፈጽመን፣ በካህኑ አማካኝነት ፍትሐት ዘወልድ ከተደገመልን በኋላ ሥጋውን ደሙን መቀበል ይገባል። አንድ ጊዜ የሠራነውን ኃጢአት ሁለተኛ ላለመሥራት በሙሉ ኀይላችን መጋደል ይገባናል።